# ባይ ባይ ሻንቆ !!

እነ ሻንቆ ይማራሉ !
ለጥሩ ውጤት ይበቃሉ !
ከሻሾ ጋር ዶክተር ፕሮፌሠር ይባላሉ !
በአስተሳሰብ ግን ይደክማሉ !
ይፈዛሉ !
ያፈዛሉ !
አይነቁም !
አያነቁም
አይደራጁም አያደራጁም
ጥቁሩ ቀለማቸውን አላስከበሩም
ለአንድነትም አልቆሙም !!
በዘር ጎሣ በሃይማኖት
በከፋፍለህ ግዛው ስሜት
ሕዝባዊነትን በላካተተ መልኩ
የዘር ጎሣ ፖለቲካ እያቦኩ !
አንዱን በሌላው አተራምሰው
ሀገር ሕዝብን መቅ አውርደው
ጉድ እየተባለ የሻንቆ ነገር !
እንደ ተአምር ሲነገር
አኅጉሪቱ ጣሯ በዝቶ
እሪታዋ በዓለም ጎልቶ
ቅጣቱ ለየትውልዱ ደርሶ
ሻንቆ ዛሬም ይኖራል አልቅሶ !
የሻንቆ ትውልድ መከራው
መቼ ይሆን መቋጫው ?

የእናት አፍሪካ ልጅ ሻንቆ
አንደበትህ ከትናጋህ ተጣብቆ !
የነፃነት ሐቅህ በውስጥህ ተደብቆ !
ዕውነትህ ብርሃን ላይ ላትወጣ
በነጫጭባው ጅራፍ ስትቀጣ !!
እስከ መቼ ይሆን ትዕግሥትህ ?
መከራ ተቀባይነትህ ?
ራስህን እያታለልህ መኖርህ ?
ነጫጭባው በተንኮሉ አድጎ !
በግፍ ሥራው በልጽጎ !
የሁሉ ነገር መለኪያው
የመነሻና መድረሻው
ቀለም ሆኖ አምልኮቱ !
ሰብዕናን አድርጎ ከንቱ
በጥፋቱ ሥልጣኔ
ብሎ ማን ይበልጣል ከኔ
ሻሾ የቀለም ማተቡን ላይበጥስ !
ዓለምን በፍቅር ላያድስ !
ሻንቆን በሻንቆ ሲያጫርስ !!
አንተም ዕውነተኛውን ነፃነት ሳትለብስ !
ዘመናት ነጎዱ ዲሞክራሲን ሳትቋደስ !!
ታዲያ ምን ይሆን አሳብህ ሻንቆ ?
ዕትብትህ ከገዥዎች ጋር ተጣብቆ
ሕይወትህ በነጫጭባው ታንቆ !
ማን ያላቅህ ምስኪኑን ሻንቆ ?
ጠላትህን ተለማምጠህ
ወገንህን አጥፍተህ
ነፃነትህን ረግጠህ
ራስህን በራስህ ስትገድል
መስሎህ የተቀዳጀህ ድል !!
ሻሾ የራሱን ሕዝብ ሲያደርግ ደስተኛ
ያንተ ሕዝብ ሁሌ ምጽዋተኛና ሃዘንተኛ !!
ኅብረት አቋቋምሁ ብለህ
የእጅ አዙር ባርነትን ተቀብለህ
ባንተነትህ አንተነትህን አንቀህ
ዕውን ይህን ስህተት ትገነዘባለህ ?

ኀብረት ተብሎ  በውጤቱ ያልረካ !
አቋቋምሁት ያልኸው ለአፍሪካ
ሻንቆን ጠባቂ መስሎ
ከሻሾ ጋር ተማምሎ
በሻሾ ትዕዛዝ ሻንቆን በሻንቆ አጫርሶ
ሠላሙን አደፍርሶ
ሕዝብን በሕማምና ስደት አቃውሶ
የአኅጉሪቱን ሀብት አስወርሶ !
ከረሃብ ብዛት ሻንቆ ጣቶቹን ልሦ
መኖርን ጠልቶ ጉድጓድ ምሶ
መቃብር ናፍቆት ለኀልፈቱ !
ምንም ሳይመስለው ሕይወቱ !
ጠላቱን ድል መንሳት ቢሳነው
ሞቶ ሞትን ድል ሊያደርገው
ሻንቆ እያለቀ ነው ከምድሩ !
ይፍረድለት እንጂ እግዜሩ !!

አታሰላም እንጂ ብታሰላው
ካንተና ከነጫጭባው
የሚያልቀው ሕዝብ በየዕለቱ
ይገባህ  ነበር  ውጤቱ !
አሁንማ ዝምታህ በጣም በዝቶ
ለሻሾ የልብ ልብ ሰጥቶ
ከነነፍስህ ሊሸጥህ
ከምድርህ ላይ ሊጠርግህ
ዝግጅቱ ተጧጡፏል !
አንተም በዝምታ ተውጠሃል !!
ጻሩ ግን ምን ያደርጋል ?
ነገር ዓለሙን ትተኸዋል !
ሻሾም ግራ ያጋባሃል !
ተስተውሎህስ ከየት ይመጣል ?
ለማንኛውም ምክሬን ከተቀበልኸው
ከልቦናህ ካስተዋልኸው
ያላንተ ማንም ስለማያግዳት
ቺቺናን ከሽሪኮቿ ጋር ዞር በይ በላት !!

አልጋ ወራሽ ቺቺና
በአፍሪካችን ልትዝናና
አኅጉራችንን ወርራ
ሻንቆን ከሀገሩ አባርራ !
ተምሮ መናው ሻንቆ
እርስ በርሱ ተናንቆ
የት ሊሄድ ነው ሀገር ለቆ ?
ልሰደድ ተብሎ ይፎከራል ?
ስደት ሆነና ቀላል ?
አይ ጉድ ! እስቲ ጉድ እንበላ !
ድንገት ቢገኝ ሌላ  መላ
መርገምተ-ሕይወት ስደት
እንዲህ በቀላል ሳያልፏት
ሀገር ጥለው ሲሰደዱ
ስንት እንቅፋት አለ በመንገዱ ?
ምን ቢደፈር ምንስ ቢባል
ስደት አይደለም ቀላል !
አይመችም አይዳላ
የሰውን ዘር እያጉላላ !!
ቀረጣጥፎ እየበላ !!
መቼም የሻንቆዬ ነገር
ተነግሮ አያልቅ ቢዘረዝር !
የራሱን ሀብት ተመጽውቶ !!
ሳይሞት በቁሙ ሞቶ
አይ አፍሪካ መዛበቻ !
የዓለማት ሁሉ መተረቻ
ሕዝቦችሽ እንግልቱ !
የማይባሉ አንቱ !

ድኅነትህንና የኢኮኖሚ ድቀትን አሳበው
ሊረዱህ ያሰቡ መስለው
በአዲስ ዘዴ ተማምለው
ጊንጦቹ በዝባዥ ኃይላት
ቺቺናን ስለፈሯት
ያንተን አኅጉር ሊክዷት
ኩታንኩት ምናምኑን
አርትፊሻል ግብስብሱን
ይዛ ብትገባም ቺቺና
መስላ አፍሪካን ልታቀና
ሻንቆዬ እንዳታምናቸው
አንተን ሊያጠፉ ነው አድማቸው
ዘወር በሉ በላቸው
ዲክታተር ላንተ ያዘነ መስሎ
ከበዝባዥ ኃይላት ጋር ተዋውሎ !
ዘመናዊውን ቅኝ-አገዛዝ በላይህ ተክሎ !
አንተንና ቤተሰብህን ከእርሻህ ነቅሎ !!
ያያቶችህ የቅድመ አያት !
የትውልድህና ያንተ ኩራት !!
የኔ አኅጉር የምትላት !
ዲክታተሩ በእጅ አዙር ሲሸጣት !!
አንተም በዝምታ ስታያት !
ነገኮ የሌሎቹ ናት !!
ባይ ! ባይ ሻንቆ !
ጠላትህ ሊያጠፉህ ነው አንቆ !
ባይ ባይ ሻንቆ ይብቃኝ እንግዲህ
ካሁን ወዲያ ምን ልንገርህ ?
በየክልል ሽምቅ ውጊያው
በጎሣ ዘር አጥፊ ፍልሚያው
በእጅ አዙሩ ሜርሲነሪ
ሲያወልቁልህ ያንተን ሱሪ
ወንድነትህ ጀግንነትህ
የአፍሪካዊነት ኩራትህ
በነጫጭባው ተሰልቦብህ
ወኔ አልባ አድርጎሃል !
ባይ ባይ ሻንቆ አልቆልሃል !!
የራስህን ሀብት ተመጽውተህ
ሳትሞት በቁምህ ሞተህ !!
አይ አፍሪካ መዛበቻ !
የዓለማት ሁሉ መተረቻ !
ሕዝቦችሽ እንግልቱ
የማይባሉ አንቱ !
ተብሎ ሲነገርልህ
ዓለማት ሲሳለቁብህ
ትንሽ ወኔም አይነሽጥህ ?
ባይ ባይ የኔው ሻንቆ !
ጠላት ሊያጠፉን ነው አንቆ !
ቀሚስ ለባሽዋ ሻንቆ እናቴ
እነሆ ላንቺ መልዕክቴ
ልጆችሽን አስታውሻቸው
ማኅጸንሽም አይዘንጋቸው
በእናትነትሽ ምከሪያቸው
ከመፃኤው አደጋ አድኛቸው
የጨካኝ ገዥዎች አድማ
አኅጉሪቱን ሳይከት ጭለማ
የማኅጸንሽ ፍሬዎች ሳይጠፉ
ሞራል ስጫቸው ይትረፉ !!
የነዚያን ለነፃነት ሲሉ ታግለው ያለፉትን
ብርቅዬ ጀግኖች ሰማዕታትን !
ይህ ትውልድ እንዳያሳፍራቸው
እንዳይወቅሰን የሰማዕታት አጥንታቸው
አጥብቀሽ ምከሪያቸው

ከአቤ ኮስትሬ